# የኢትዮጵያ ኦርቶዶስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ሃይማኖትና ሥርዓት
# The Ethiopian Orthodox Tewahido Church Faith and Order

www.ethiopianorthodox.org

## ምስጢረ ጥምቀት

**ጥያቄ፡-ምስጢረ ጥምቀት ማለት ምን ማለት ነው?**

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ስለመሠረተው ሥርዓተ ጥምቀት የምንማረው ትምህርት ምስጢረ ጥምቀት ይባላል።

**ጥያቄ፡-ጥምቀት ማለት ምን ማለት ነው?**

ጥምቀት ማለት መላው ሰውነት በውኃ መንከር ወይም ማጥመቅ ማለት ነው።
በግእዝ ልሳን «አጥመቀ አጠመቀ ነከረ» ካለው ግስ ጥምቀት የተባለው ቃል ተገኘ።

**ጥያቄ፡- ጥምቀትን የጀመረው ማነው?**

እውነተኛዋን ጥምቀት የጀመረ ወይም የመሠረተው ጌታችን እየሱስ ክርስቶስ ነው።

**ጥያቄ፡-ጌታችን እየሱስ ክርስቶስ እውነተኛዋን ጥምቀት የመሠረተው ወይም የጀመረው መቼ ነው?**

ጌታችን እየሱስ ክርስቶስ ከቅድስት ድንግል ማርያም በድንግልና ተፀንሶ በድንግልና ተወልዶ ዕድሜው ሠላሳ ዓመት ያህል ሲሆነው በዮርዳኖስ ወንዝ በዮሐንስ እጅ ተጠመቀ (ሉቃስ ፫፡ ፳፩-፳፫)።

የጌታችን ጥምቀት ታሪክ ባጭሩ እንዲህ ነው፤ «ያን ግዜ ኢየሱስ በዮሐንስ ሊጠመቅ ከገሊላ ወደ ዮርዳኖስ መጣ ዮሐንስ ግን እኔ በአንተ ልጠመቅ ያስፈልገኛል፤አንተ ግን ወደ እኔ ትመጣለህ? ብሎ ከለከለው ኢየሱስም መልሶ አሁንስ ተው እንዲህ ጽድቅን ሁሉ መፈጸም ይገባልና አለው። ያን ግዜ ፈቀደለት። ኢየሱስ ከተጠመቀ በኃላ ወዲያው ከውኃ ወጣ እነሆም ስማያት ተከፈቱ፤ የእግዚአብሔር መንፈስ እንደ ርግብ ሲወርድ በእርሱም ላይ ሲቀመጥ አየ፤ እነሆም ድምፅ ከስማይ መጥቶ በእርሱ ደስ የሚለኝ የምወደው ልጄ ይህ ነው አለ» (ማቴ ፲፫፤፲፯)። ማርቆስ፤ ሉቃስና ዮሐንስም የጥምቀቱን ታሪክ ከማቴዎስ ጋር አስማምተው መዝግበውታል፤ (ማር ፩፥፱-፲፩  ሉቃ ፫፥፳፩-፳፫ ዮሐ ፩፡ ፴፪-፴፬)።

**ጥያቄ፡-ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በማየ ዮርዳኖስ በእደ ዮሐንስ ሲጠመቅ የተፈጸሙ ታሪኮች ምንና ምን ናቸው?**

ጌታችን ሲጠመቅ የተፈጸሙት አስደናቂ ስራዎች ከዚህ የሚከተሉት ናቸው፡-

፩ ስማያት ተከፈተዋል (ሲከፈቱ ታይተዋል)፤
፪ መንፈስ ቅዱስ በርግብ አምሳል ወርዶ በኢየሱስ ራስ ላይ ረቦ ሲያርፍ ታይቶአል፤
፫ እግዚአብሐር አብ የምወደው ልጄ(የባህርይ ልጄ) ይህ ነው ብሎ ድምጹን አስምቶ መስክሮለታል፤
፬ በቅዱስ ዳዊት የተነገረው ትንቢት ይፈጸም ዘንድ ጌታችን ይጠመቅ ዘንድ ዮርዳኖስ በሄደ ግዜ የዮርዳኖስ ወንዝ ባልተለመደ ሁኔታ ሲጨነቅ፤ ከቦታው ለመሸሸ ሲሞክር ታይታል። ዮርዳኖስ ወራጅ ውኃዎች ሁሉ ፈርተዋል፤ በዚህ ግዜ ቅዱስ ዳዊት በመንፈስ ቅዱስ ተመርቶ(ተቃኝቶ)፣ «ባህር አይታ ሸሸች ዮርዳኖስም ወደ ኃላው ተመለሰ» ሲል የተናገረው ትንቢት ተፈጸመ (መዝ. ፻፲፫፥(፻፲፬) ፫-፭)

## <u>ጥያቄ</u>፦ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ለምን በዮርዳኖስ ተጠመቀ?

፩. ከዚህ በላይ የተጠቀሰው ቅዱስ ዳዊት የተናገረው ትንቢት ይፈጸም ዘንድ፤
፪. ዮርዳኖስ ለጥምቀት ታሪካዊ ምሳሌነት ያለው በመሆኑ፤
፫. ዮርዳኖስ ለምስጢረ ሥላሴ ምስጢራዊ ምሳሌ ያለው በመሆኑ፤
፬. በቤተክርስቲያን የትውፊት ማለት የሥርዓትና የባህል መጸሕፍት እንደተመዘገበው፣ ዲያብሎስ በዮርዳኖስ ባሕር የደበቀውን የአዳምንና የሔዋንን የባርነት ደብዳቤ ይደመስስ ዘንድ ጌታችን በዮርዳኖስ ወንዝ ተጠመቀ።

## <u>ጥያቄ</u>፦ዮርዳኖስ ለአማናዊቱ ማለት ለእውነተኛይቱ ጥምቀት ታሪካዊ ምሳሌነት አለው የተባለው እንዴት ነው?

ዮርዳኖስ ጥምቀት ታሪካዊ ምሳሌነት አለው የተባለው፦

1. መስፍኑ እያሱ ለእስራኤል ልጆች ምድረ ርስትን ለማካፈል ወደ ምድረ ከነዓን ለመሻገር ከእስራኤል ልጆች ጋር ከዮርዳኖስ ወንዝ በደረሰ ግዜ፣ ሞልቶ የነበረው ዮርዳኖስ ጎድሎ ግራና ቀኝም ቆሞ እያሱና የእስራኤል ልጆች እንደ ተሻገሩ ታሪኩ እንዲህ ሲል ያቀርበዋል።

«እንዲህ ሆነ ህዝቡ ዮርዳኖስ ሊሻገሩ ከየድንኳናቸው በወጡ ግዜ፣የቃል ኪዳኑን ታቦት የተሸከሙ ካህናት ከህዝቡ ፊት ፊት ይሄዱ ነበር። እንደ መከርም ወራት ሁሉ ዮርዳኖስ እጅግ ሞልቶ ነበር ታቦት የተሸከሙት ካህናት ወደ ዮርዳኖስ ሲደርሱ እግራቸውም በውኃው ዳር ሲጠልቅ፣ ከላይ የሚወርደው ውኃ ቆመ፤ በጻርታን አጠገብ ባለችው አዳም በምትባል ከተማ በሩቅ ቆሞ እንደ አንድ ክምር ተነሳ፤ ወደ ዓረባ ባሕር (ወደ ጨው ባሕር) የሚወርደው ውኃ ፈጽሞ ተቋረጠ፤ ህዝቡም በኢያሪኮ ፊት ለፊት ተሻገሩ። የእግዚአብሔር የቃል ኪዳን ታቦት የተሸከሙ ካህናት በዮርዳኖስ መካከል በደረቅ መሬት ጸንተው ቆመው ነበር። ሕዝቡም ዮርዳኖስን ፈጸመው እስኪሻገሩ ድረስ እስራኤል ሁሉ በደረቅ መሬት ተሻገሩ። በታሪኩ መሠረት ዮርዳኖስ የእውነተኛይቱ ጥምቀት ምሳሌ ነው። ኢያሱ የጌታችን ምሳሌ ካህናቱ የሐዋርያትና የአርድእት ምሳሌ ታቦቱ የሕገ ወንጌል ሕዝበ እስራኤል ምእመናን ምሳሌ ናቸው።

ኢያሱ ዮርዳኖስን አሻግሮ ምድረ ርስትን ለሕዝበ እስራኤል እንዳወረሳቸው፣ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስም ምእመናንን በጥምቀት ወደ መንግሥተ ስማያት አሻግሮ ርስተ መንግስተ ስማያትን የማውረሱ ምሳሌ ነው።

2. የሶርያው ንጉሥ ሠራዊት አዛዥ የነበረው ንዕማን፣ አካሉ ሁሉ በለምጽ ደዌ ስለ ተበከለ በሽተኛ ሆኖ ሲኖር ሳለ፣ በነብዩ በኤልሣዕ ትእዛዝ በዮርዳኖስ ወንዝ ተጠምቆ ከለምጹ እንደተፈወሰ ታሪኩ እንዲህ ተብሎ ተመዝግቦአል፤ «ንዕማን ሶርያዊ በፈረሱና በሠረገላው መጥቶ ከኤልሣዕ ቤት ደጃፍ ውጪ ቆመ። ኤልሣዕም ሂድ በዮርዳኖስን ሰባት ግዜ ታጠብ፤ ከደዌህ ትፈወሳለህ፤ አንተም ንጹሕ ትሆናለህ ብሎ መልክተኛ ላከ። ንዕማን ግን ተቆጥቶ ሄደ፤ እንዲህም አለ፦ እነሆ ነቢየ እግዚአብሔር ወደኔ መጥቶ ከፊቴ ቆሞ፤ የእግዚብሔርን ስም ጠርቶ፤ ለምጽ ያለበትንም ገላዬን በእጁ ዳስሶ የሚፈውሰኝ መስሎኝ ነበር እንጂ የውኃ ውኃማ የደማስቆ ወንዞች አባባና ፋርፋ ከእስራኤል ውኃዎች ሁሉ አይበልጡምን? በእነርሱስ ውስጥ መታጠብና መንጻት አይቻለኝም ኖሮአልን? ብሎ ወደ ሀገሩ ለመመለስ ፊቱን መለሰ። ነገር ግን አሽከሮቹ ቀርበው አባት ሆይ፤ ነቢዩ ታላቅ ነገርስ ቢነግርህ ኖሮ ባደረግከው ነበር፤ ይልቁንስ ነቢዩ ታጠብና ንጹሕ ሁን ሲልህ እንዴት እሺ ብለህ አትታጠብም? ብለው ነገሩት። እርሱም ወርዶ የእግዚያብሔር ሰው ኤልሣዕ እንደነገረው በዮርዳኖስ ሰባት ግዜ ብቅ ጥልቅ እያለ ታጠበ፤ ገላውም ገና እንደ ትንሽ ወጣት ገላ ሆኖ ተመለሰ፤ ከደዌውም ተፈወሰ፤ ንጹህም ሆነ» (፪ነገሥ. ፭፥፱-፲፬)።

በታሪኩ መሠረት ዮርዳኖስ የጥምቀት ምሳሌ፣ ኤልሣዕ የጌታችን፣ ንዕማን የምእመናን ምሳሌ፣ ለምጽ የኃጢአት፣ የመርገመ ሥጋ፣ የመርገመ ነፍስ ምሳሌ፣ ንዕማን በኤልሳዕ ትእዛዝ በዮርዳኖስ ታጥቦ ከለምጹ እንደተፈወሰ፣ በጌታችን የሚያምኑ ምእመናንም በጌታችን ትእዛዝ በአብ በወልድ በመንፈስ ቅዱስ ስም ተጠምቀው ከኃጢአት፣ ከበደል ንጹሕ ይሆናሉ። በዚሁ መሠረት ዮርዳኖስ ለእውነተኛዋ ጥምቀት ታሪካዊ ምሳሌ ነው የተባለው ስለዚህ ነው። እንደዚሁም ዮርዳኖስ ለሰው ልጆች የመሠረት አንድነት ምሳሌ ነው። ይኸውም ዮርዳኖስ ከላይ ነቅዑ (ምንጩ) አንድ ነው። በመካከል ሲደርስ በ

ትንሽ ደሴት ተከፍሎ ይፈሳል፤ ከታች ወርዶ ይገኛል። ነቅዑ አንድ እንደ ሆነ፣ የሰው ሁሉ አባት አንድ አዳም ነው።ከመካከል በደሴት ተከፍሎ እንዲፈስስ እስራኤል በግዝረት፣ በኦሪት፣ አሕዛብ ባለ መግረዝ (በቁልፈት) በጣዖት ተለያይተው ይኖሩ ነበርና በኋላ ጌታችን በሠራት ጥምቀት ሁሉም አንድ ሕዝብ ሆነዋል።

## <u>ጥያቄ</u>፦«ዲያብሎስ ዮርዳኖስ ወንዝ የደበቀው የዕዳ ደብዳቤ ይደመሰስ ዘንድ፣ በዮርዳኖስ ተጠመቀ» የተባለው እንዴት ነው?

በመጽሐፈ ቀሌምንጦስ እንደ ተጻፈ፣ አዳምና ሔዋን ከገነት ተሰደው በደብር ቅዱስ ሳሉ፣ ዲያብሎስ በድንገት መጥቶ የጨለማ መጋረጃ ጋርዶ ሥቃይ አጸናባቸው፤ ወዲያው በምትሐት ጥቂት ብርሃን መሰል ነገር የያዘ መስሎአቸው፣ ይህንን ጨለማ አርቅልን አሉት። ስም ግብርናችሁን (የባርነታችሁን ስም) ጻፉችሁ ስጡን እና ላርቅላችሁ አላቸው። እነሱም መከራው የቀለላቸው መስሎአቸው፣ «ይሁንብን፣ ጻፍብን» አሉት። እርሱም፣ «አዳም ገብሩ ለዲያብሎስ፣ ሔዋን ዓመቱ ለዲያብሎስ» ብሎ በሁለት ዕብነ ሩካብ ቀርጾ አንዱን በዮርዳኖስ፣ አንዱን በሲኦል መካከል ደብቆት ነበርና ጌታችን በኪደተ እግሩ በዮርዳኖስ የተደበቀውን ደብዳቤ ለማጥፋት በዮርዳኖስ ተጠመቀ። በሲኦል የተደበቀውንም በዕለተ ዓርብ ደምስሶታል። «ወደመሰሰ ለነ መጸሐፈ ዕዳነ፤ በትእዛዛት የተጻፈውን የእዳ (የበደል) ደብዳቤ ደመሰሰልን» እንዳለ ቅዱስ ጳውሎስ (ቆላ.፪፥፲፬)።

## ጥያቄ፦ ጌታችን ምንም ዓይነት በደልና ኃጢአት የሌለበት ቅዱስ አምላክ መሆኑ የታመነ ነው፤ ነገር ግን ለምን ተጠመቀ?

<u>መልስ</u>፦ ጌታችን የተጠመቀው ለሶስት ነገር ነው፤ ይኸውም፦

፩. ከላይ እንደ ተነገረው፣ በዮርዳኖስ ወንዝ የነበረው የዕዳ (የበደል) ደብዳቤ ለመደምሰስ፤

፪. በመጠመቁ አርአያ ሆኖ ሥርዓተ ጥምቀትን ለእኛ ለመስጠት፤

፫. ውኃዎችን (ወንዞችን) ለመባረክና ለመቀደስ።

ይህንን ምስጢር አስመልክቶ ቅዱስ ጎርጎርዮስ ዘእንዚናዙ ስለ ወልደ እግዚአብሔር በጻፈው ሐተታ፣ ቁጥር 2/፪ ላይ እንዲህ ብሎአል፤ «እርሱ ሰው እንደ መሆኑ ተጠመቀ፤ አምላክ እንደመሆኑ ኃጢአትን ደመሰሰ። ንጽህናን ሽቶ የተጠመቀ አይደለም፤ እርሱ ንጽሕ እምንጹሓን ነውና፤ ነገር ግን ውኃውን ለመባረክና የውኃውን ባህርይ ለመቀደስ ተጠመቀ እንጂ» ብሎአል።

ሳዊሮስ ዘአንጾኪያም፣ «አኮ ፈቂዶ ለተጠምቆ ሐሰ፤ ወዳእሙ ከመ ያስተርኢ ወሀበነ ጥንተ ልደት ዳግማየ፤ ወውእቱስ አልቦቱ መፍቅድ በኀቤነ ለነ ለእጓለ እመሕያው» ብሎአል። ይኸውም፣ «ጥምቀት ሽቶ አይደለም፤ ረብ ጥቅም ለማግኘት አልተጠመቀም፤ አምላክ በሥጋ ተገልጦ ጥንተ ልደትን ዳግመኛ ይሰጠን ዘንድ ነው እንጂ፤ እርሱስ ከእኛ ከሰዎች ዘንድ የሚሻው ነገር የለም» ማለት ነው (ሃይማኖተ አበው፣ ገጽ ፫፻፷፭ ቁ.፩፭)።

## <u>ጥያቄ</u>፦ጌታችን በዮርዳኖስ በተጠመቀ ግዜ የተገለጸው ታላቅ ምስጢር ምንድን ነው?

ጌታችን በዮርዳኖስ በተጠመቀ ግዜ ምስጢረ ሥላሴ (የእግዚአብሔር የሦስትነት ምስጢር) እውን ሆኖ ተገልጾአል።

ይኸውም
፩ ከሦስቱ አካላት አንዱ እግዚአብሔር ወልድ በለበሰው ሥጋ በማየ ዮርዳኖስ በእደ ዮሐንስ ተጠመቀ፤

፪ ወልድ በሰውነቱ ዮርዳኖስ ተጠምቆ ከውኃ ሲወጣ፣ ስማይ ተከፍቶ መንፈስ ቅዱስ በርግብ አምሳል ወርዶ በጌታችን ራስ ላይ ተቀመጠ።

፫. እግዚአብሔር አብ በሰማይ፤ «የምወደው ልጄ ይህ ነው» ብሎ የወልድን ባሕርይ ልጅነት መሰከረ ለት (ማቴ. ፫-፲፯፤ ማር. ፩ ፱-፲፪፤ ሉቃ ፫ ፳፩-፳፪ ዮሐ. ፩-፫፪)።

በዚሁ ምስጢረ ጥምቀት አማካኝነት፣ የሦስቱ አካላት መገለጽ ግልጽ ሆኖ ታውቆአል። እንደዚሁም፤ «ዝንቱ ውእቱ ወልድየ ዘአፈቅር ዘቦቱሠመርኩ፤ በእርሱ ደስ የሚለኝ የምወደው ልጄ ይህ ነው» ብሎ እግዚአብሔር አብ በመመስከሩ፣ እምቅድመ ዓለም ከአብ የተወለደው፣ በኋላኛውም ዘመን ከቅድስት ድንግል ማርያም በድንግልና የተወለደው እግዚአብሔር ወልድ ተቀዳሚና ተከታይ የሌለው አንድ ብቻ መሆኑ ተረጋግጦአል።

ቅዱስ ቄዎርሎስና ቅዱስ ሳዊሮስ ዘአንጾኪያም ምታዌንና ኅድረትን ያስተማሩትን መናፍቃን በማሳፈር፣ «ወእይቤ አብ በላእለ ዝንቱ ወልድየ፣ አላ ይቤ ዝንቱ ውእቱ ወልድየ፤ በተዋሕዶ አንድ አካል አንድ ባሕርይ አድርጎ የምወደው ልጄ ይህ ነው አለ እንጂ፣ በዚህ አድሮ ያለው ልጄ ነው አላለም» ብለው አስተምረዋል (ትርጓሜ ወንጌል ማቴ. ፫፤፲፯)።

## <u>ጥያቄ</u>፦እኛ ሰዎች በውኃ የምንጠመቀው ለምንድን ነው?

እኛ ሰዎች በውኃ የምንጠመቅበት ዋናው ቁም ነገር በሚከተለው ምክንያት ነው፦ የመጀመሪያው አባታችን አዳም የእግዚአብሔር ትእዛዝ ስላፈረሰ በሞተ ሥጋ ሞተ ነፍስ፤ በርደተ መቃብር ርደተ ገሃነብ ተፈረደበት ይህም የሞት ፍርድ ለልጆቹ ሁሉ አለፈ (ሮሜ. ፭ ፲፭-፳፭)፤ ስለዚህ ሰውሁሉ ከውኃና ከመንፈስ ካልወለደ በቀር ወደ ገነት፣ ወደ መንግሥተ ስማያት መግባት የማይችል ስለሆን ከውኃና ከመንፈስ ቅዱስ ለመወለድ በውኃ እንጠመቃለን።

## <u>ጥያቄ</u>፦ከውኃና ከመንፈስ ቅዱስ መወለድ ማለት ምን ማለት ነው?

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ፍጹም አምላክና ፍጹም ሰው መሆኑን ያመነ፣ እንደዚሁ እርሱ ብቻ የዓለም መድኃኒት እንደሆነ በፍጹም ልቡ ያመነ ሰው ሁሉ፣ በአብ፣ በወልድ፣ በመንፈስ ቅዱስ ሰም በውኃ በተጠመቀ ጊዜ ወድያውኑ በረቂቅ ሁኔታ(በማይታይ ሁኔታ) ከመንፈስ ቅዱስ ይወለዳል። ይኸውም በጥምቀት፣ ጸጋ መንፈስ ቅዱስን ተቀብሎ በጸጋ የእግዚአብሔር ልጅ ይሆናል ማለት ነው። ይህንን ታላቅ ምስጢር ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ኒቆዲሞስ ለተባለው የአይሁድ መምህር ለመጀመሪ ጊዜ ተገልጾለት ነበር። ታሪኩም እንዲህ ነው «...ኢየሱስም መልሶ ለኒቆዲሞስ፦ እውነት እውነት እልሃለሁ ሰው ዳግመኛ ካልተወለደ በቀር የእግዚአብሔርን መንግሥት ሊያይ አይችልም አለው። ኒቆዲሞስም መልሶ፦ ሰው ከሸመገለ በኋላ እንዴት ሊወለድ ይችላል? ሁለተኛ ወደ እናቱ ማኅፀን ገብቶ ይወለድ ዘንድ ይችላልን? አለው። ኢየሱስም መልሶ እንዲህ አለው፦ እውነት እውነት እልሃለሁ፦ ሰው ከውኃና ከመንፈስ ቅዱስ ካልተወለደ በቀር ወደ እግዚአብሔርን መንግሥት ሊገባ አይችልም። ከሥጋ የተወለደ ሥጋ ነው፤ ከመንፈስ የተወለደ መንፈስ ነው። ዳግመኛ ልትወለዱ ያስፈልጋችኃል ስላልሁህ አታድንቅ። ነፋስ ወደሚወደው ይነፍሳል፤ ድምፁንም ትሰማለህ ነገር ግን ከየት እንደ መጣ ወዴትም እንደሚሄድ አታውቅም፤ ከመንፈስ የተወለደው ሁሉ እንዲሁ ነው» (ዮሐ. ፫፤፫-፱)

አሁን ከዚህ በላይ እንደ ተገለጸው፣ ለኒቆዲሞስ፣ ዳግመኛ መወለድየሚባለው አነጋገር ሊገባው ወይም ሊረዳው አልቻለም። ምክንያቱም ኒቆዲሞስ በተለመደው መንገድ ከአባት ከእናት መወለድ እንጂ፣ ከመንፈስ የመወለድ ነገር አያውቅም ነበርና። ጌታችን ግን ይህንን ታላቅ ምስጢር መረዳት ላቃተው ለኒቆዲሞስ ከውኃና ከመንፈስ መወለድ ማለት ምን ማለት እንደሆነ የንፋስን ጉዞ ምሳሌ አድርጎ አስረድቶታል፤ ስለዚህ ጌታችን ባስተማረው መሠረት፤ ማንኛውም ሰው ወደ መንግሥተ ስማያት መግባት ይችል ዘንድ በሥርአተ ጥምቀት ከውኃና ከመንፈስ ቅዱስ መወለድና በጸጋ የእግዚአብሔር ልጅ መሆን ይገባዋል።

**<u>ጥያቄ፦</u>ከዚህ በላይ ከተመለከትነው ሌላ ጌታችን እየሱስ ክርስቶስ ስለ ጥምቀት አስፈላጊነት ያዘዘው ትእዛዝ አለን?**

አዎን አለ፣ ጌታችን እየሱስ ክርስቶስ ላመነ ለማንኛውም ሰው ጥምቀት እጅግ አስፈላጊ በመሆኑና ያለ ጥምቀት በጸጋ የእግዚአብሔር ልጅ መሆንና ወደ መንግሥተ ስማያት መግባት የማይቻል ስለሆነ፣ ጌታችን እየሱስ ክርስቶስ ሞትን ድል አድርጎ ከሙታን ተለይቶ ከተነሣ በኋላ ለቅዱሳን ሐዋርያት እንዲህ ሲል አዞአቸዋል፣ «እንግዲህ ሂዱና አሕዛብን ሁሉ አስተምሩ በአብ በወልድ በመንፈስ ቅዱስ ስም እያጠመቃችኋቸው፣ ያዘዝኋችሁንም ሁሉ እንዲጠብቁ እያስተማራችኋቸው ደቀ መዛሙርት አድርጓው» (ማቴ. ፳፰፥፲፱-፳)። እንደገናም እንዲህ አላቸው «ወደ ዓለም ሁሉ ሂዱ፤ወንጌልንም ለፍጥረት ሁሉ ስበኩ፤ ያመነ የተጠመቀ ይድናል፤ ያላመነ ግን ይፈረድበታል» (ማር. ፲፮፥፲፮)።

**<u>ጥያቄ፦</u>ጌታችን ለእኛ አርአያውን (ምሳሌውን) ይንጠን ዘንድ በዮርዳኖስ ውኃ መጠመቁን ከፍ ብለን ተመልክተናል፤ ነገር ግን በጌታችን ያመኑ ሰዎች የተጠመቁበት ውኃ ምን ዓይነት ነው?**

ጌታችን እየሱስ ክርስቶስ ለምእመናን ሥርዓተ ጥምቀትን ከሠራበት ቀን ጀምሮ ምእመናን የተጠመቁበትንና እኛም የተጠመቅንበትን ውኃ በዕለተ ዓርብ ከጌታችን ጎን የፈሰሰው ውኃ ነው። እንደሚታወቀው፤ ጌታችን እየሱስ ክርስቶስ ለመላው የሰው ልጅ ሕይወት፣ ድኅነትን ለመስጠት ሲል በዕለተ ዓርብ በፈቃዱ መከራን ተቀብሎ በመስቀል፣ በለበሰው ሥጋ ከሞተ በኋላ፤ እርሱን ከሰቀሉት ወገኖች አንዱ ጐኑን በጦር በወጋው ጊዜ ወዲያውኑ ደምና ውኃ ፈሷል (ዮሐ. ፲፱፥፴፬)። ምስጢሩ እንደዚህ ነው፦ የጌታችን አገልጋዮች ቀሳውስት፣ ምእመናንን ለማጥመቅ ሲፈልጉ ውኃውን በብርት፣ ወይም በገንዳ፣ ወይም በትልቅ ስነብርት (ስሐን) ሞልተው ተገቢውን ሥርዓተ ጸሎት ያደርሱበታል፣ ከዚያም አስፈላጊውን ቡራኬ ከፈጸሙበት በኋላ ውኃው በመንፈስ ቅዱስ ኀይል ተለውጦ ከጌታችን ጎን የፈሰሰውን ቅዱስ ውኃ ይሆናል። በዚህ ጊዜ በዚያ ውኃ የተጠመቀ ሁሉ፣ በጸጋ ከአብ ከወልድ ከመንፈስ ቅዱስ ይወለዳል፣ በጸጋም የእግዚአብሔር ልጅ ይሆናል።

**<u>ጥያቄ፦</u>ጥምቀት በግድ አስፈላጊ ነውን?**

አዎን በጥምቀት ከውኃና ከመንፈስ ቅዱስ ካልተወለዱ በቀር ወደ እግዚአብሔር መንግሥት መግባት አይቻልምና ጥምቀት እጅግ አስፈላጊ ነው (ዮሐ. ፫፥ ፭-፯)።

**<u>ጥያቄ፦</u>ከጥምቀት የሚገኙት ጥቅሞች ምንና ምን ናቸው?**

ከጥምቀት የሚገኙ ጥቅሞች የሚከተሉት ናቸው።
፩ ስርየተ ኃጢአትን ማግኘት፣ ማለት ከማንኘውም ኃጢአት ንጹሕ መሆን፤
፪ ከመንፈስ ቅዱስ ዳግመኛ በመወለድ፣ በጸጋ የሥላሴ (የእግዚአብሔር) ልጅ መሆን፤
፫ መንግሥተ ስማያትን ለመውረስ በመንፈስ ቅዱስ መታተም ናቸው።

ጌታችን እየሱስ ክርስቶስ የመሠረታት ጥምቀት ኃጢአትን የምታስተሰርይና ድኅነትን የምታስጥ ታላቅ ምስጢር መሆንዋን ቅዱስ መጽሐፍ ያረጋግጣል። በጥምቀት ድኅነተ ነፍስ እንደሚገኝ ጌታችን ራሱ፣ «ያመነ የተጠመቀ ይድናል» ሲል አሰተምሮአል (ማር.፲፮፤፲፮)። ሐዋርያው ቅዱስ ጴጥሮስም በበዓለ ኀምሳ ለተሰበሰቡ ሰዎች፣ «ንሰሐ ግቡ፤ኃጢአታችሁ ይስረይ ዘንድ እያንዳንዳችው በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ተጠመቁ፤ የመንፈስ ቅዱስንም ሰጦታ ትቀበላላችሁ»ሲል አሰተምሮአቸዋል(የሐዋ. ፪፣፴፰)። ሦስት መቶ አሥራ ስምንቱ ቅዱሳን አበውም በቀኖና ሃይማኖት፣ «ኃጢአት በሚሰረይባት በአንዲት ጥምቀት እናምናለን»ብለዋል(ጸሎተ ሃይማኖት)።

## ጥያቄ፦ጥምቀት ስንት ግዜ ትፈጸማለች?

በአብ በወልድ በመንፈስ ቅዱስ የምትፈጸም ጥምቀት አንዲት ናት።አንድ ግዜ ከተፈጸመች ማለት ከተሰጠች በኋላ አትደገምም። በካህን በኤጲስ ቆጶስ እጅ የምትፈጸምው ጥምቀት አንዲት ናት። «ሊቀ ጳጳሳት ወይም ጳጳስ ወይም ኤጲስ ቆጶስ ሳይመጣ አናጠምቅም አይበሉ፤ የማጥመቅ ሥልጣን ያለው ያጥምቅ እንጂ፤ የጥምቀት ሥልጣን አንዲት ናትና» ተብሎ በሕገ ቀኖና ታዞአልና (አንቀጽ ሣልስ፣ቁ.፴፱)።

## ጥያቄ፦ጥምቀት በስንት ትከፈላለች?

ከዚህ በላይ እንደ ተገለጸው፣ አማናዊቷ ማለት እውነተናዋ ጥምቀት አንዲት ናት። ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ጥምቀት አንድ መሆንዋን ሲመሰክር፣ «አንድ ጌታ፣ አንዲት ሃይማኖት፣ አንዲት ጥምቀት፣ ከሁሉ በላይ የሚሆን፣ በሁሉም የሚሠራ፣ በሁሉ የሚኖር አንድ አምላክ የሁሉ አባት አለ» ብሎአል (ኤፌ. ፬፣፬-፮)።

በሌላ በኩል ግን ጌታ የመሠረታት ጥምቀት አንዲትና የማትደገም መሆንዋ የታወቀ ቢሆንም፣ ጥምቀትን የሚመስሉ አራት ዓይነት መንገዶች እንዳሉ ቅዱስ ጎርጎርዮስ ዘእንዚናዙ ገልጾአል። ይህ ቅዱስ አባት ስለ ምስጢራተ ቤተክርስቲያን በጻፈው ክፍል ሲገልጽ እንዲህ ብሎአል፦

፩. ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ እንደ ጻፈው (፩ቆሮ. ፲፣፪)፣
እስራኤላውያን ከደመና በታች ሆነው ባሕር ሲሻገሩ ሁሉም በደመናና በባሕር ተጠመቁ...... ያለው እንደ ጥምቀት ይቆጠራል፣ ግን ምሳሌ እንጂ አማናዊ ጥምቀት አይደለም። ምሳሌነቱም፣ ባሕር አማናዊቱ ጥምቀት ምሳሌ፣ ደመና የመንፈስ ቅዱስ ምሳሌ፣ መና የኅብስተ ሕይወት (ቅዱስ ቁርባን) ምሳሌ፣ የጠጡት መንፈሳዊ ውኃም የክርስቶስ ደም ምሳሌ ነው፤

፪. ዮሐንስ መጥምቁ ሲያጠምቃት የነበረች ጥምቀት ናት፤ ነገር ግን ዮሐንስ ለንስሐ በውኃ ብቻ እንጂ በመንፈስ ቅዱስ ሰላላጠመቀ፣ የዮሐንስ ጥምቀት የንስሐ እንጂ አማናዊት ጥምቀት አልነበረችም።

፫. በስማዕትነት ደምን በማፍሰስ የምትፈጸም ጥምቀት ናት። ይህች ጥምቀት ክርስቶስን መምስልን የምታስጥ እጅግ የከበረች ጥምቀት ናትና ዋጋዋ ከፍ ያለ ነው።

፬. «አንብዐ ንስሓ» ማለት በንስሐ ግዜ የሚፈስው የለቅሶ፣ የሐዘን እምባ ነው። የንስሐ እንባ ለስርየተ ኃጢአትን ስለሚስጥ እንደ ጥምቀት ይቆጠራል (ድርሳነ ጎርጎርዮስ፣ ኦሬንቴሽን ፴፱-፲፯)፤

ከነዚህ ከዚህ በላይ የተገለጹት የጥምቀት መንገዶች ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የመሠረታትን ጥምቀት የሚመስሉ ናቸው።በተለይም በሦስተኛውና በአራተኛው ተራ ቁጥር የተገለጹት የጥምቀት መንገዶች የእውነተኛዋን ጥምቀት የሚያህሉ ናቸው።

## ጥያቄ፦ክርስቶስን አምነው በስማዕትነት ደማቸውን አፈስሰው ከሞቱና ከሚሞቱት ቅዱሳን ሰዎች በቀር፣ ሁላችንም የክርስቶስን ሞት የምንሳተፍበት ምስጢር የትኛዋ ናት?

የክርስቶስን መከራና ምት የምንሳተፍባት ምስጢር ጥምቀት ናት፤ ስለዚህም ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ በሮም ለነበሩ ምእመናን በጻፈው መልእክቱ በጥያቄ መልክ እንዲህ ሲል አስረድቶአቸዋል፤ «ወይስ ክርስቶስ ኢየሱስ ጋር አንድ እንሆን ዘንድ የተጠመቅን ሁላችን ከሞቱ ጋር አንድ እንሆን ዘንድ እንደ ተጠመቅን አታውቁምን?» ብሎአል (ሮሜ ፮፥፫)። ለገላትያ ምእመናን በጻፈውመልእክቱም፣ «በእምነት በኩል ሁላችሁ በክርስቶስ ኢየሱስ የእግዚአብሔር ልጆች ናችሁና፤ ከክርስቶስ ጋር አንድ ትሆኑ ዘንድ በክርስቶስ የተጠመቃችሁ ሁሉ ክርስቶስን ለብሳችኋልና።

አይሁዳዊ ወይም አረማዊ ሰው የለም፤ ባሪያ ወይም ጨዋ የለም፤ ወንድ ወይም ሴት እየተባባሉ መለያየት የለም፤ ሁላችሁ በክርስቶስ ኢየሱስ አንድ ናችሁና» ሲል አስረድቶአል (ገላ.፫ ፳፮፥፳፱)።

ራሱ ጌታችን በዕለተ ዓርብ የተቀበለውን መከራ «ጥምቀት» ብሎ ሠይሞታል(ማቴ. ፳፥፳፪)፤ ስለዚህ በአብ በወልድ በመንፈስ ቅዱስ ስም የምንጠመቃት ጥምቀት፣ ዳግመኛ መወለድንና በጸጋ የእግዚአብሔር ልጅ መሆንን የምታስጥ ከመሆንዋም በላይ፣ ከክርስቶስ ጋር የመሞታችንን፣ የመቀበራችንን ጒልህ ምሳሌ መሆንዋንም መገንዘብ ተገቢ ነው። «ወተጠምቆትነሰ በማይ፣ ውእቱ ተሳትፎትነ በሞተ ክርስቶስ፤ ወዕርገትነሂ እምነ ማይ ውእቱ ካዕበ አምሳለ ተንስኦትነ ምስሌሁ፤ በውኃ መጠመቃችን በክርስቶስ ሞት አንድ የመሆናችን ከውኃ መውጣታችን ሁለተኛ ከእርሱ ጋር የመነሳታችን ምሳሌ ነው» ተብሎ በህገ ቀኖና (በፍትህ መንፈሳዊ) ተደንግጎአል (አንቀጽ ሣልስ ቁ. ፳፯ ድስቅ)።

## ጥያቄ፦ሥርዐተ ጥምቀት የሚፈጸመው እንዴት ነው?

ለመጠመቅ የሚመጡ ሰዎች ወንድ የጐለመሰ ከሆነ፤ ሴቲቱም ያደገች ከሆኑ፣ በቅድሚያ የእግዚአብሔርን አንድንነት ሦስትነት ጠንቅቀው ሊያስተምሩአቸው ይገባል። ለመጠመቅ የመጡ አማንያን ትምህርተ ክርስትናን ተምረው በሚገባ ካወቁ በኋላ ያጥምቋቸው። ሲያጠምቋቸውም መላ ሰውነትን የሚያጠል ውኃ መሆን ይገባል። አጥማቂው ካህን ተመማቂውን(ተመማቂዋን) በውኃው ሦስት ግዜ ብቅ ጥልቅ እያደረገ በአብ በወልድ በመንፈስ ቅዱስ ያጠምቀዋል (ያጠምቃታል)። ምሳሌውም ከላይ እንደተገለጸው ተመማቂው ከውኃው ሦስት ግዜ ብቅ ጥልቅ ብሎ መጠመቁ፣ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሦስት መዓልት ሦስት ሌሊት በከርሠ መቃብር አድሮ፣ ሞትን ሽሮ፣ የመነሳቱ ምሳሌ ነው (ሮሜ. ፮ ፫-፭)። በሕገ ቀኖና (በፍትሕ መንፈሳዊ) እንደታዘዘው፣ ጥምቀት በወራጅ ውኃ ወይም በሚፈስ ውኃ ይሁን። በዚያ የውኃ ችግር ቢኖር ያገኙትን ውኃ ቀድተው ወደ ማጥመቂያው ያፍስሱ(አንቀጸ ሣልስ፣ በስ.፻፯)። በዚሁ ቀኖና «በስ» በሚል ምሕፃረ ቃል የተመዘገበው ሕገ ቀኖና ዘባስልዮስ ማለት ነው። በቀኖናው መሠረት በጥምቀት ጊዜ ተጠማቂውን ሰው በሙሉ የሚያጠልቅ የታቆረ ውኃ፣ የገንዳ ወይም ኩሬ ውኃ የማይገኝ ከሆነ፣ አጥማቂው ኤጲስ ቆጶስ ወይም ካህን ውኃውን በእጁን እያፈሰሰ በአብ በወልድ በመንፍስ ቅዱስ ስም በተጠማቂው ራስ ላይ ሦስት ግዜ እያፈሰሰ እንዲያጠምቅ መታዘዙ በቂ ውኃ ሳይገኝ ሲቀር ነው፤ በቂ ውኃ በሚገኝበት አካባቢ ግን ተመማቂውን ሰው በሙሉ የሚያጠልቅ ውኃ ማጥመቅ የሚገባ መሆኑ ከፍ ብሎ ተገልጾአል።

ተጠማቂው ሰው ሥርዓተ ጥምቀት ከተፈጸመለት በኃላ በመጽሐፈ ክርስትና እንደ ታዘዘው፣ ቅብዓ ሜሮን ይቀቡታል፤ ከዚያም ፀዓዳ ልብሰ ማለት ነጭ ልብስ ያለብሱታል፤ ወዲያውም ቅዱስ ቍርባን ያቆርቡታል። ከቆረበም በኋላ በመጀመሪያ ቀዝቃዛ ውኃ፣ ከዚያም ወተትና ማር ይሰጡታል፤ ይህ ሥርዓት በጥንቷ ቤተክርስቲያን ማለት ከሁለተኛው፣ ከሦስተኛው ካራተኛው ክፈለ ዘመን ጀምሮ የተለመደ የቤተክርስቲያን ሥርዓት እንደነበረ ስለ ሥርዓተ ጥምቀት የተጻፈው የጥንቱ ሕገ ቀኖና (ሕገ ቤተክርስቲያን) ያስረዳል (የሀዋርያት ቀኖና፣ አንቀጽ ፳፪-፳፬)።

## ጥያቄ፦ሕፃናት በሕፃንነት ዕድሜያቸው ጥምቀተ ክርስትናን እንዲቀበሉ (እንዲጠመቁ) ማድረግ የሚገባን ነውን?

አዎን፤ ሕፃናትን ማጥመቅ የሚገባ ነው። ጥምቀት ለክርስትና ሃይማኖት «መግቢያ በር» መሆንዋ የታወቀ ነውና፤ ሕፃናት የቤተክርስቲያንልጆችና የምእመናን ማኅበር አባላት መሆን የሚችሉት በጥምቀት ስለሆነ መጠመቅ ያስፈልጋቸዋል።

**ከትምህርተ ሃይማኖት ኦርቶዶክሳዊት** 1991 **አቡነ ገብርኤል ከጻፉት የተወሰደ።**

## የሕፃናት ጥምቀት

በቤተክርስቲያናችን ሁለት የጥምቀት ዘመናት አሉ። እነርሱም የሕፃናትና የትልልቆች የጥምቀት ዘመን በመባል ይታወቃሉ። እድሜያቸው ለአቅመ አዳምና ሄዋን ከደረሱ በኃላ የሚጠመቁት ጥምቀት የትልል ቆች ጥምቀት ይባላል። ይህም ሚስጢረ ጥምቀት ለመፈጸም የሚያስፈልጉ ነገሮች በሚለው ርዕስ የተገ ለጹ ስለሆነ አሁን የሕፃናትን ጥምቀት እንመለከታለን። ቅድስት ቤተክርስቲያናችን ለምስጢረ ጥምቀት አፈጻጸም ብርቱ ጥንቃቄ ታደርጋለች። ሰው ሁሉ በጥምቀት አማካኝነት የሚሰጠውን ጸጋ እንዲያገኝ አ ስፈላጊውን ጥረት ሁሉ ትፈጽማለች። ሰዎች ሳይጠመቁ እንዳይሞቱ በማለት ሕፃናትን እንዲጠመቁ ታ ስተምራለች ታጠምቃለችም። ሕፃናትን የምታጠምቀው በቅዱሳት መጻሕፍት በቅዱሳን አበው ትውፊትና ሥርዓት መሠረት ነው። ሕፃናትን የምታጠምቀው ከቅዱሳት መጻሕፍት በተረዳችው መሠረት እንደሆነ ከዚህ ቀጥለን ለማየት እንሞክራለን።

1.0 በመጽሐፈ ኩፋሌ ም. 4 ቁ. 9 ላይ «ከተፈጠረባት ምድር ለአዳም አርባ ቀን ከተፈጸመለት በኃላ ይገዛትም ይጠብቃትም ዘንድ ወደ ገነት አስገባነው። ሚስቱንም በሰማንያ ቀን አስገባናት።» ይላል። ለአዳምና ሔዋን ንፅሐ ጠባይዕ ሳያድፍባቸው ከመንፈስ ቅዱስ የጸጋ ልጅነት ተቀብለው በመላእክት ታጅበው በ40ና በ80 ቀን ገነት እንደገቡ ዛሬም ወንድ ልጅ በተወለደ በ40 ቀኑ ሴት ልጅ በተወለደ ች በ80 ቀኗ በጥምቀት አማካይነት ከእግዚአብሔር ተወልደው ገነት መንግሥተ ሰማያት እንዲገቡ ታደርጋለች። ምንም እንኳ ልደተ አዳም ከምድር፣ ልደተ ሔዋን ከአዳም ጎን ሆኖ በሕፃናት መጠ ን ባይፈጠሩም ማለትም አዳም የ30 ዓመት ጎልማሳ ሔዋን የ15 ዓመት ቆንጆ ሁነው ቢፈጠሩም ያ ቺ የተፈጠሩባት ዕለት ካለመታየት ወደ መታየት የመጡባት ሰብአዊ ፍጡርነታቸው የታወቀባትና የ ተረጋገጠባት ዕለት በመሆኗ እንደ ልደት ቀን ትቆጠራለች። ሕፃናትም ቢሆኑ በማኅፀን ሳሉ አይታዩ የነበሩ ወደ መታየት የሚመጡትና ሰው መሆናቸው የሚታወቀው በልደታቸው ዕለት ነው። ስለዚህ አዳምና ሔዋን በተፈጠሩ በ40ና 80 ቀናቸው በክብር ወደ ገነት እንደገቡ ዛሬም ቅድስት ቤተክርስ ቲያን እግዚአብሔር መጀመሪያ በሠራው ሥርዓት መሠረት በአዳም አለመታዘዝ ምክንያት የተወሰደ ውን ልጅነት ለማስመለስ ሕፃናት ወንዶችን በ40 ቀን ሕፃናት ሴቶችን በ80 ቀን ዕድሜያቸው ታጠ ምቃለች።

2.0 እግዚአብሔር የአብርሃምን የይስሐቅንና የያዕቆብን ልጆች ከአሕዛብ ለይቶ የተመረጠ ሕዝብ ካደረ ጋቸው በኋላ የሚመሩበት ሕግ ሰጥቷቸዋል። ከእነዚህም መካከል በዘሌዋውያን 12፥1-8 የሚገኘው ነው። እስራኤላውያን በመንፈሰ ረድኤት የእግዚአብሔር በረከት እንዲያድርባቸው የእግዚአብሔር ሕዝብ/ወገን/ መሆናቸው እንዲረጋገጥ ወንድ ልጅ በተወለደ በ40ቀኑ ሴት ልጅ በተወለደች በ80 ቀ ኗ ወላጆቻቸው መሥዋዕት ይዘው ወደ ቤተ መቅደስ ይወስዷቸው ነበር። ካህናቱም መሥዋዕቱን ሠ ውተው ሕፃናቱን በእግዚአብሔር ስም ባርከው ስማቸውን በመዝገብ አስገብተው ይሰዷቸው ነበር። እንደ ኦሪቱ ሕግ የተፈጸመለት ሕፃን የፈጣሪን በረከት ከማግኘቱም በላይ የእግዚአብሔር ሕዝብ ወ ይንም ወገን ይሆናል። እንደዚሁም ቤተክርስቲያን ሕፃናቱን በ40 ቀንና በ80 ቀን አጥምቃ የእግዚአ ብሔር ወገን ታደርጋለች። በዘመነ ኦሪት ሕፃናቱ በወላጆቻቸው እምነት መሥዋዕት ተሰውቶላቸው የእግዚአብሔር ወገን እንደሚሆኑ በዘመነ ሐዲስም ሕፃናት በወላጆቻቸው እምነት ወደ ቤተክርስቲያ ን ተወስደው በጥምቀት የእግዚአብሔር የጸጋ ልጆች ይሆናሉ። በዚህም ሕጻናት መሥዋዕተ ሐዲስ የሆነውን የክርስቶስ ሥጋና ደም ተቀብለው የእስራኤል ዘነፍስ የቤተክርስቲያን አባልና አካል ይሆና ሉ።

3.0 በብሉይ ኪዳን ዘመን አብርሃም እግዚአብሔርን አምኖ ከዘመዶቹ ተለይቶ አምላኩን ከተከተለ በኋ ላ እግዚአብሔር የቃል ኪዳን ምልክት ሰጠው። ይህም የቃል ኪዳን ምልክት በእግዚአብሔርና በአ ብርሃም በዘሩም መካከል የዘላለም ምልክት ስለሆነ ማናቸውንም ወንድ ልጅ በተወለደ በ8ኛው ቀን እንዲገረዝ ታዟል። ትልልቅ ሰዎችም በልጅነታቸው ካልተገረዙ ካደጉ በኃላ ይገረዛሉ አብርሃም ሲ ገረዝ የ99 ዓመት ሽማግሌ ነበር። እስራኤል በ13 ዓመቱ ተገርዟል። ይስሐቅ ግን በተወለደ በስምን ተኛው ቀን ተገርዟል።እግዚአብሔር አምላክ የዚህን ቃል ኪዳን ጽኑነት «የቁልፈቱን ሥጋ ያልተገረ ዘ ቆላፍ ሰው ሁሉ ያቺ ነፍስ ከወገኗ ሁሉ ተለይታ ትጥፋ ቃል ኪዳኔን አፍርሳለችና» በማለት ገል ጿል። ዘፍ. 17፥1-5

በሐዲስ ኪዳን ግዝረት የጥምቀት ምሳሌ እንደሆን ቅዱስ ጳውሎስ በቆላ. 2፥11-12ላይ «የሥጋንም ሰውነት በመግፈፍ በክርስቶስ መገረዝ በእጅ ባልተደረገ መገረዝ በእርሱ ሆናችሁ ደግሞ የተገረዛችሁ በጥምቀት ከእርሱ ጋር ተቀበራችሁ» በማለት ጥምቀት በክርስቶስ አማካኝነት የሚፈጸም ሕመም የሌለው ከመርገምና ከኃጢያት ቁልፈት የምንለይበት ግዝረት እንደሆነ ገልጿል። በኦሪቱ ሕፃናትም አዋቂዎችም ተገርዘው እግዚአብሔር ለአብርሃም የሰጠውን ተስፋ ወራሾች እንደሚሆኑ ሁሉ ዛሬም ሕፃናትንም አዋቂዎችንም በማጥመቅ የቤተክርስቲያን አባል የክርስቶስ አባል እንደ ተስፋ ቃሉ የመንግሥተ ሰማያት ወራሾች ይሆናሉ። ያልተገረዘ ሰው ከወገኑ ከእስራኤላውያን ተለይቶ እንደሚጠፋ ዛሬም በሐዲስ ኪዳን ያልተጠመቀ ሰው ከክርስቲያኖች ተለይቶ በገሃነም እሳት ይጠፋል ወደ መንግሥተ ሰማያት መግባት አይችልም።

4.0 ቅዱስ ጳውሎስ በ1ኛ ቆሮ. 10፥1-2 ላይ«ወንወድሞች ሆይ ይህን ታውቁ ዘንድ እወዳለሁ አባቶቻችን ሁሉ ከደመና በታች ነበሩ ሁሉም በባሕር መካከል ተሻገሩ ሁሉም ሙሴን ይተባበሩ ዘንድ በደመናና በባሕር ተጠመቁ» ብሎ በመጻፍ የእስራኤላውያን ቀይ ባሕርን መሻገር የጥምቀት ምሳሌ እንደሆነ ገልጿልናል። እስራኤላውያን ከፈርኦን ባርነት ከግብጽ የመከራ ቦታ በእግዚአብሔር ኃይል ነጻ ከወጡ በኃላ ወተትና ማር ወደምታፈሰው ሀገር ለመጓዝ ቀይ ባሕርን መሻገር ነበረባቸው። ቀይባሕር እስራኤላውያንንሲያሻግር ግብጻውያንን አስጥሟል። በቀይ ባህር መካከል የተሻገሩት እስራኤላውያን አዋቂዎች ብቻ አልነበሩም ሕፃናትም አብረው ተሻግረዋል ቀይ ባሕርን በተአምራት እንደተሻገሩ፣ ጠላቶቻቸው እንደሰጠሙ፣ የአምላክን ድንቅ ሥራና ኃይል የሙሴን ባለሟልነትና ንግግር የሰሙትና ያዩት ትላልቆቹ ናቸው። ሕፃናቱ ግን በወላጆቻቸው አማካይነት ከተሻገሩ በኃላ ነፍስ ሲያውቁ እግዚአብሔር በዘጠኝ መቅሰፍት በአሥረኛ ሞተ በኩር በአሥራ አንደኛው መቅሰፍተ ስጥመት ጠላቶቻቸውን አጥፍቶ፣ ባሕሩን ከፍሎና ደመና ጋርዶ እንዳሻገራቸው የነገራቸውንአምነው ከመቀበል በቀር የሚያረጋግጡበት ሌላ መንገድ የላቸውም። ሕፃናቱም አዋቂዎችም እኩል ተሻግረዋል። ሕፃናቱ በልጅነታቸው ሳያውቁና ሳይረዱ በቀይ ባሕር መሻገራቸው ትክክል አይደለምና እስኪያድጉ ድረስ በበረሃ ይቀመጡ አይባልምና ወይም በሕፃንነት ሳላውቅ የተሻገርኩት መሻገር ስህተት ነውና አሁን ሳውቅ ስረዳ እንደገና ቀይ ባሕርን ልሻገር ቢል አይችልም። ቀይ ባሕርን አንዴ የተሻገረ ለምንጊዜም ተሻገረ እንግዲህ በሐዲስ ኪዳንም ያለው የጥምቀት ሥርዓት ከዚህ ታሪክ ጋር የተያያዘ ነው። ተነፃፃሪም ነው። እስራኤል ዘነፍስ ከሲያል ግብጽ ከፈርያን ዲያቢሎስ ከግብጻውያን አጋንንት በክርስቶስ መሪነት ነጻ ወጥተው ወደ ሰማያዊት እየሩሳሌም ለመግባት የግድ ከጥምቀቱ በቀይ ባሕር በኩል መሻገር /ማለፍ/ አለባቸው ጥምቀት ክርስቲያኖች ከፈጣሪያቸው የጸጋ ልጅነት የሚያገኙበት ከሰይጣን ነጻ የሚወጡበት ሲሆን በአንጻሩ ኃጢያታቸውም መርገመ ሥጋ መርገመ ነፍስ እንደ ፈርያንና ሠራዊቱ በጥምቀት ይደመሰሳል። አዋቂ ሳለ የተጠመቀም በሕፃንነቱ የተጠመቀ ውጤቱ አንድ ነው። በሕፃንነቱ የተጠመቀ ሰው መጠመቁን ወላጆቹና የክርስትና አባቱ የሚነግሩትን አምኖ በመቀበል ለምግባር ለትሩፋት መነሳሳት አለበት እንጂ እንደገና እጠመቃለሁ ማለት የለበትም። የእስራኤላውያን ሕፃናት ቀይ ባሕርን አንዴ ብቻ ከተሻገሩ ከዛም በኋላ መሻገር እንደማይችሉ ይህም ሕፃን አንድ ጊዜ ስለተጠመቀ ዳግም መጠመቅ አያስፈልገውም። አንድ ጊዜ የተጠመቀ ለምንጊዜውም ተጠምቋል።

5.0 በዘፍ. 7፥1 ላይ እንደምንረዳው «እግዚአብሔር ኖህን አለው አንተ ቤተሰቦችህን ሁሉ ይዘህ ወደ መርከብ ግባ በፊቴ ጻድቅ ሆነህ አይቼሃለውና» በማለት በመርከቡ አማካይነት ከጥፋት ውሃ ኖህን ከነቤተሰቡ ሊያድነው እንደወደደ እንረዳለን። ኖህ በትእዛዙ መሠረት ቤተሰቦቹን ሁሉ ይዞ ወደ መርከብ እንደገባ በዘፍ. 7፥17 ተገልጿል። ኖህ ቤተሰቦቹ ለእግዚአብሔር ቃል ታዛዥ ሆነው በመርከቡ ውስጥ እንደገቡ ከጥፋት ውኃም እንደዳኑ ተረድተናል። ኖህ ሦስቱ ልጆቹ ማለትም ሴም፣ ካምና ያፌት ሕፃናት ቢሆኑ ኖሮ ወደ መርከቡ እንዳይገቡ ያግዳቸው ነበርን? የኖህ ልጆ ሕፃናት ልጆች ቢኖርዋቸው ኖሮ ሕፃን ስለሆኑ ከመርከብ ውጪ ይተዋቸው ነበርን? እግዚአብሔርን በሃይማኖት ያላወቁና ያላመኑ ለድህነት የተዘጋጀውን መርከብ አይተው ያልተረዱ በመርከብ ውስጥ ለመግባትም ሆነ ላለመግባት በራሳቸው ፈቃድ መወሰን የማይችሉ ሕፃናት ቢኖሩ ኖሮ አድገው የፈጣሪን መኖር አውቀው አምነው ለድኅነት የተዘጋጀውን መርከብ አይተው ወደ መርከቡ ለመግባት በራሳቸው ነፃ ፈቃድ እስኪወስኑ ድረስ ከመርከብ ውጪ የሚያቆይ ወላጅ ይኖር ይሆንን? ምንም ያልበደሉ ሕፃናት በጥፋት ውሃ እንዲጠፉ ከመርከብ ውጪ የሚያስወጣቸው ሰው እውነተኛ ወላጅም ጤነኛ መሆኑ ያጠራጥራል። እግዚአብሔር ኖህን ያዘዘው ቤተሰቡን ይዞ ወደ መርከብ እንዲገባ ነው። ማንም እንዳይጠፋ የእግዚአብሔር ፈቃድ ነውና።

ኖህ ከጥፋት ውኃ የዳነበት መርከብ የጥምቀት ምሳሌ እንደሆነ ቅዱስ ጴጥሮስ በ1ኛ ጴጥ. 3፥20-2
2ላይ ገልጾታል። በመርከቡ ውስጥ ኖህ ከነቤተሰቡ እንዲገባ እንደታዘዘ ዛሬም ከነቤተሰባችን እንድ
ንጠመቅ ቤተክርስቲያን ታዛለች። በእግዚአብሔር ዘንድ ከፊል ድኅነት የለም። ኖህ መላውን ቤተሰ
ብ ይዞ ወደ መርከቡ እንደገባ ዛሬም በኖህ አንፃር የሚገኙ ወላጆች ቤተሰባቸውን በሙሉ ሕፃናትን
ም ሳይቀር ማስጠመቅ አለባቸው። ሕፃናትን ከጥምቀት መከልከል ማለት ልጅን ከመርከብ ውስጥ
አውጥቶ የጥፋት ማዕበል ውስጥ መወርወር ነው። ይህም በእውነተኛ ዳኛ በእግዚአብሔር ያስጠይ
ቃል።

ጌታ«ሰው ዳግመኛ ከውኃና ከመንፈስ ቅዱስ ካልተወለደ በቀር ወደ እግዚአብሔር መንግሥት ሊገባ
አይችልም» ብሏል።/ዮሐ.3፥8/ የመዳን ወይም የድኅነት ትርጉምና የመጨረሻ ግቡ የእግዚአብሔር
ን መንግሥት መውረስ ነው።/1ኛ ቆሮ. 2፥9 ማቴ.25፥3/ የዘላለም ሕይወት የሚባለውም ሞት በሌለ
በት መንግሥተ ሰማይ መንግሥተ ሰማይ የሚኖረው ኑሮ ነው። /ራዕይ 21፥1-4/ ይህንን የዘለዓለም
ሕይወት የሚገኝበትን ቦታ ለመውረስ ሰው ሁሉ መጠመቅ አለበት። ይህ ግድ ከሆነም ምንም ያልበ
ደሉ ክፋትም የሌለባቸው ሕፃናት ዳግመኛ ተወልደው/ተጠምቀው/ የእግዚአብሔር የጸጋ ልጆች እን
ዳይሆኑ የሚከለክላቸው ማን ነው? መንግሥተ ሰማያት የአዋቂዎች ብቻ ሳትሆን የሕፃናትም ስለሆነ
ች ሕፃናት ይድኑ ዘንድ መጠመቅ ይገባቸዋል። መድኃኒታችን በመስቀል ላይ የተሠዋው በአካል ላ
ደጉ በዕድሜ ለበለጸጉ ብቻ አይደለም። ሕፃናትም የዚህ መሥዋዕትነት ተጠቃሚዎች ናቸው።

የክርስቶስ ሞት ለሁሉ ነውና ክርስቶስ የተሰዋላቸውን ሕፃናት አላወቁም አላመኑም ተብሎ ከበረከተ
ጥምቀት መለየት በሰው ነፍስ ላይ የሚፈጸም ረቂቅ ወንጀል ነው ከላይ እንደተጠቀሰው እስራኤላ
ውያን ልጆቻቸውን ወደ ቤተመቅደስ ወስደው መስዋዕት ሲሰውላቸውና ስያስባርካቸው ሕፃናቱ ምን
ም አያውቁም።የሕጻናቱ ምንም አለማወቅ በረከታቸውን አላስቀረውም። ሕፃናቱም ሲገረዙ እንደሌላ
ው እስራኤላዊ የእግዚአብሔር ወገን ሆኑ እንጂ የእግዚአብሔር ሕዝብ ከመሆን አላገዳቸውም። ዛ
ሬም በሕፃንነታቸው ሲጠመቁ አለማወቃቸው በጥምቀት የሚያገኙትን ጸጋ አያሳጣቸውም። ከእግዚ
አብሔርም መወለዳቸውን አያስቀርባቸውም። ስለዚህ እንደ እግዚአብሔር ቃል ዳግመኛ እንዲወለ
ዱ ወደበቤተክርስቲያን ወስዶ ማስጠመቅ የክርስቲያን ወላጅ መንፈሳዊ ግዴታ ነው።

6.0 እግዚአብሔር አምላክ ሕፃናትን ከጸጋው አያርቃቸውም። ከበረከቱም አይነፍጋቸውም ገና በእናታቸ
ው ማኅፀን ሳሉ የተቀደሱና ሀብተ መንፈስ ቅዱስ ያደረባቸው ሰዎች በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ይገ
ኛሉ። ለምሳሌ ነብዩ ኤርምያስ ገና በእናቱ ማኅፀን ሳለ እግዚአብሔር እንደ ቀደሰው ሲገልጽ «የእ
ግዚአብሔርም ቃል ወደ እኔ እንዲህ ሲል መጣ በሆድ ሳልሠራው አውቄሃለሁ ከማኅፀንም ሳትወጣ
ቀድሸሃለው ለአሕዛብም ነብይ አድርጌሃለው።» ኤር. 1፥4-5 በማለት ጽፏል።
በተመሳሳይም ሁኔታ መጥምቁ ዮሐንስም ገና በእናቱ ማኅፀን መንፈስ ቅዱስ እንደሚሞላበት ቅዱስ
ገብርኤል ለአባቱ ለዘካርያስ ሲያበስረው «ገናም በእናቱ ማኅፀን ሳለ መንፈስ ቅዱስ ይሞላበታል።»
በማለት ነግሮታል። ሉቃ. 1፥15 ይህም ትንቢት መፈጸሙን በሉቃስ 1፥42-45 ላይ እናነባለን። ስለዚ
ህ እግዚአብሔር ሕፃናትን በማኅፀን ሳሉ የሚቀድሳቸው መንፈስ ቅዱስ የሚያሳድርባቸው ከሆነ ከተ
ወለዱ በኃላ እንዳይጠመቁ የሚከለክላቸው ማነው? በቅዱስ ወንጌል ተጽፎ እንደምናገኘው ፈጣሪያ
ችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ለሕፃናት ልዩ ትኩረት በመስጠት አቅርቧቸው፣አቅፏዋቸውና
እጁን ጭኖ እንደባረካቸው ተጽፏል። በጊዜው የነበሩ ወላጆችበአሪቱ ልማድ ልጆቻቸውን ለማስባረ
ክ ወደ ጌታ ይዘዋቸው ሲመጡ ሐዋርያት ወላጆቹን ተቆጡዋቸው ሕፃናቱንም ከለከሏቸው። ጌታች
ን ግን ሐዋርያት የሠሩትን አይቶ በዝምታ አላለፈም። «ሕፃናትን ወደ እኔ ይመጡ ዘንድ ተው አት
ከልክሏቸው የእግዚአብሔር መንግሥት እንደዚህ ላሉት ናትና» በማለት እስከ ምፅዐት ለሚነሱ ሕፃ
ናት ወደ ፈጣሪያቸው ቀርበው በረከት እንዳያገኙ ለሚያግዱ ወላጆች ማስጠንቀቂያ ከሰጠ በኃላ አ
ቀፋቸው እጁንም ጭኖ ባረካቸው ይላል። /ማቴ. 19፥13-15 ማር. 10፥13-16 ሉቃ. 18፥15-17/ በወ
ላጆች እምነት ልጆች መባረካቸውን ልብ እንበል። እንግዲህ ባለቤቱ ሕፃናትን ከበረከቱ ካልነሳቸ
ው ከአጠገቡ ከአላራቃቸው ተጠምቀው ጸጋ መንፈስ ቅዱስ እንዳይቀበሉ የሚከለክላቸው ማነው?

7.0 ቅዱሳን ሐዋርያት በጥንተ ስብከት ሰዎችን አስተምረው አሳምነው ያጠምቁ ነበር። የቤተሰቡ ኃላፊ አምኖ ሲጠመቅ ቤተሰቡ በሙሉ ይጠመቅ እንደነበረ ተጽፎአል። የቤተሰብ ኃላፊ እንደ አንድ ራስ ሲሆን ሌላው ቤተሰብ እንደቀረው አካል ነው። ራስ ሲጠመቅ የቀረው አካል እንደማይለይ የቤተሰቡ ኃላፊ ሲጠመቅ መላው ቤተሰብ ይጠመቅ ነበር። ቤተሰብ የሚለው ቃል የእድሜና የጾታ ልዩነት ሳይኖር በአንድ ቤተሰብ ሥርና ስም የሚተዳደሩ ሰዎችን ያጠቃልላል። እስራኤሎች በቤተሰብ ይኖሩ ነበር። በአንድ ቤት ውስጥ የሚኖሩ ሰዎች ሁሉ ቤተሰብ ይባላሉ።/ዘፍ.12፥1/ አብርሃም ብዙ ቤተሰብ ቢኖረውም እግዚአብሔር ቃል ኪዳን የገባው ከአብርሃም ጋር ነው። በረከቱ ግን ለቤተሰቡሁሉ ነው። /ዘፍ.14፥14፣17፥9-10/ በዚሁ መሠረት ሐዋርያት የቤተሰብን ኃላፊ/አስተዳዳሪ/ ባጠመቁ ጊዜ መላው ቤተሰብም ይጠመቅ ነበር። ቤተሰብ ውስጥ ከሕፃን እስከ አረጋዊ ድረስ ስለሚገኝ ሁሉም የዕድሜ ገደብ ሳያግዳቸው ይጠመቃሉ። በሐዋ.ሥራ 2፥38 ላይ ቅዱስ ጴጥሮስ «ንስሐ ግቡ ኃጢያታችሁ ይሰረይ ዘንድ እያንዳንዳችሁ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ተጠመቁ የመንፈስ ቅዱስንም ጸጋ ትቀበላላችሁ የተስፋው ቃል ለእናንተና ለልጆቻችሁ ጌታ አምላካችንም ወደ እርሱ ለሚጠራቸው በሩቅ ላሉ ሁሉ ነው።»በማለት ጥምቀት፣ ጸጋ መንፈስ ቅዱስና የተስፋ ቃል ለአዋቂ ብቻ ሳይሆን ለሕፃናትም እንደሚታደል ገልጿል። ለምሳሌ በሐዋ.ሥራ 10፥44-48 እና 11፥13-14 ቆርኔልዮስ ከነቤተሰቡ በም.16፥15 ላይ ሊድያ ከነቤተሰብዋ በ16፥43-44 የእስር ቤቱ ዘበኛ ከመላ ቤተሰቡ ጋር እንዲሁም በ1ኛ ቆሮ.1፥16 የእስጢፋኖስ ቤተሰብ እንደ ተጠመቁ ተጽፎ ይገኛል። እነዚህ ቤተሰብ ውስጥ ሕፃናት የሉም ማለት ሐሰተኝነት ነው። ሕፃናት መጠመቅ የለባቸውም ማለት ደግሞ በመጽሐፍ ቅዱስ ያልተጻፈን ማገበብና ኢክርስቲያናዊነት ነው።

በእነዚህና እነዚህን በመሳሰሉት ምክንያቶች ቤተክርስቲያናችን ሕፃናትን በአርባና በሰማንያ ቀን ታጠምቃለች። በፍትሐ ነገሥት አንቀጽ ሦስት ላይ ቅዱሳን አባቶች «ጥምቀት የተሠራው ለወንዶችም ለሴቶችም ለትልልቆችም ለትንንሾችም ነው» ማለታቸው ከቅዱስ መጽሐፍ በመረዳታቸውና የቅዱሳን ሐዋርያት ተከታዮች በመሆናቸው ነው። ስለዚህ ወንድ በ40 ቀን ሴት በ80 ቀን እንዲጠመቁ ታዟል። ነገር ግን ሕፃኑ ወይም ሕፃኗ ለሞት የሚያሰጋቸው ሆኖ ከተገኘ ከ40 ቀን በፊት መጠመቅ ይችላሉ። ሕፃኑ ሳይጠመቅ ቢሞት የካህን ጥፋት ከሆነ ከሥልጣነ ክህነት እንዲሻር ጥፋቱ በወላጆች ከሆነ ለተወሰነ ጊዜ ከምእመናን እንዲለዩ ያደርጋል። ፍትሐ ነገሥት መንፈሳዊ አንቀጽ 3. ሕፃናት የዘላለምን ሕይወት እንዲያገኙ የወላጆችና የቤተክርስቲያን ፍላጎት ነው። ያለጥምቀት ደግሞ ዘላለማዊ ሕይወት አይገኝም ቤተክርስቲያን ሕፃናት በወላጆቻቸው እምነት የተነሳ የወላጆቻቸውን እምነት የእነሱ እምነት በማድረግ ሕፃናትን ከእግዚአብሔር መንግሥት ውጪ እንዳይሆኑ ታጠምቃለች ። ሕፃናት በመጠመቃቸው የቤተክርስቲያንን ሕይወት ይለማመዳሉ።

(ብኩርና ከሚለዉ በመምህር ጥበበ ሥላሴ ከጻፉት የተወሰደ, 1992)
*ምሥጋና ይሁን ለአብ ለወልድ ለመንፈስ ቅዱስ ዛሬም ዘወትርም ለዘለዓለሙ አሜን።*